# የሲፒጄ ገመና ሲገላለጥ

ዲበኩሉ 12/31/13

የጋዜጠኞች መብት ተከራካሪ ድርጅት ብሎ ራሱን የሰየመው ሲፒጄ ከሰሞኑ ኢትዮጵያ የጋዜጠኞችን መብት በማፈን  በዓለም ሁለተኛ ናት ሲል መግለጫ አውጥቷል፡፡ ይህ ሙያዊ ሳይሆን ፖለቲካዊ መግለጫ አስገራሚ ቢሆንም በውስጡ ብዙ መሰሪ ሴራዎችን ያቀፈ ነው፡፡ ቀጣዩ የአምስት ዓመት ብሔራዊ ምርጫ እየተቃረበ ከመሄዱ አንጻር ከወዲሁ እየተጠነሰሰና እየተሰራ ያለውን የእነ ሲፒጄ፣ አይ ፒ አይ ፣ አምነስቲ ኢንተርናሽናል፣ ሂዩመን ራይትስ ዎች፣ ኢንተርናሽናል ሪቨርስና የመሳሰሉትን የታቀደና የተጠና ጸረ ኢትዮጵያ ዘመቻ በገሀድ ያሳያል፡፡

ሁሉም በየፊናቸው በተለያዩ ርዕሶች የሚያወጡት መግለጫ በውንጀላ የተሞላ የሆነበት ምክንያት ምንድነው ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው፡፡ እነዚህ ተቋሞች በመሰረታዊ ዓላማና ግብ አንድ ናቸው፡፡ በስም የተለያዩ ቢሆኑም የምዕራቡን ዓለም የናጠጡ ዓለምአቀፍ ከበርቴዎች በተለይም የኒዮ ሊበራል ሀይሎች ጥቅም ማስከበሪያ መሳሪያና ድምጽ በመሆን ይሰራሉ፡፡ የእነሱን የኒዮሊበራል የገበያ ፍልስፍናና የከበርቴውን ቅጥያጣ ዓለምአቀፍ ምዝበራን የሚቃወሙ መንግስታትንም ሆኑ ድርጅቶች ያወግዛሉ፣ይወነጅላሉ፡፡  ብሔራዊ አህጉራዊና ዓለምአቀፋዊ የተፈጥሮ ሀብቶችን ለመመዝበር በተለያዩ ሽፋን የተሰማሩ የምእራቡ አለም ተቋማትና ድርጅቶችጋር እጅ ለእጅ ተያይዘው ይሰራሉ፡፡

ሲፒጄ የፕሬስ ነጻነትን በማፈን ኢትዮጵያን ከኤርትራ ቀጥሎ ሁለተኛ አገር አድርጎ ሲያስቀምጥ ይህ ተቋም ምን ያህል በስህተት የተዘፈቀና በመሳሪያነት ለሚያገለግላቸው ወገኖች ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ፍላጎት የመጨረሻውን ትግል እያደረገ መሆኑን ያሳያል፡፡ ኢትዮጵያን ምንም አይነት የፕሬስ ነጻነትም ሆነ የግል ፕሬስ ከሌላት፤ የተቃዋሚ ፓርቲ አንድም በሕጋዊ መንገድ ከሌላት፤ የነጻ ገበያ ኢኮኖሚ ከማትከተለውና ሲቪል መሰል የወታደራዊ አምባገነን አገዛዝ ከሰፈነባት፤ በቅርብና በሩቅ ለአሸባሪ ሀይሎች ልዩ እገዛና እርዳታ በወታደራዊ መስክም ሆነ በስልጠና ከምትሰጠው ይህም በመንግስታቱ ድርጅት አጣሪ ቡድን በተደጋጋሚ ከተረጋገጠባት ኤርትራ ጋር  ኢትዮጵያን መፈረጁ የሲፒጄን የከፋ ጥላቻና መሰሪነት ያሳያል፡፡

ሲፒጄ በሁለንተናዊ መልኩ ስለፈጣን የኢኮኖሚ እድገቷ  በምዕራቡ መንግስታት፣  ዓለም ባንክ፡ አይኤምኤፍ፡  በተደጋጋሚ ስለተመሰከረላት ኢትዮጵያ አንድም መልካምና በጎ ጎን ማንሳት አይፈልግም፡፡ እንደ ሌሎቹ መሰል የዓላማ ተጋሪ ተቋሞቹ ሁሌም የሚጠመደው በክስ ውንጀላና ስም ማጥፋት ዘመቻ ነው፡፡

በኢትዮጵያ የፕሬስ ነጻነት በመኖሩ ነው በርካታ የግል ጋዜጦችና መጽሔቶች እየታተሙ ለንባብና ለገበያ የሚቀርቡት፡፡ ከዚህ ቀደም የነበሩት በርካታዎችም ከገበያ የወጡት በመንግስት ጫና ሳይሆን አቅም በማጣትና ስራቸውን ለማካሄድ ባለመቻላቸው ነው፡፡ በጋዜጠኝነታቸው ሳይሆን በሌላ ሁኔታ ሕግና ደንብ ከሚፈቅደው ውጭ የተንቀሳቀሱ በሀገሪቱ ሕግ መሰረት እንዲጠየቁ መደረጋቸው በኢትዮጲያ ብቻ ሳይሆን በየትኛውም ዓለም የሚሰራበት የተለመደ አሰራር ነው፡፡

ሲፒጄ እንደሚሰብከው ልቅና በስርአተ አልበኛነት የተሞላ ዲሞክራሲና የፕሬስ ነጻነት በየትም አለም የለም፡፡ የሀገሪቱን ሰላምና ደህንነት የሚያናጋ ተቻችሎ የኖረውንና የሚኖረውን ሕብረተሰብ የሚያጋጭና የሚያጣላ፡ ሁከትና አመጽ እንዲቀሰቀስ በዚህም የህዝብ ሰላም ደፍርሶ ደም እንዲፋሰስ ለማድረግ የሚንቀሳቀሱ ግለሰቦችንም ሆነ የግል ፕሬሶችን በፕሬስ ነጻነት ስም ጥፋትና ውድመት እንዲያመጡ በመረንነት መልቀቅ፣ እንዳሻችሁ ፈንጩ ማለት ፈጽሞ አይቻልም፡፡ እንዲህ አይነት ነጻነት በአሜሪካም በእንግሊዝም ሆነ በዬትም የለም፣ ሊኖርም አይችልም፡፡

ይህን የሚሰሩ የነበሩ ግለሰቦችን ነው ለምን በሕግ ተጠየቁ፤ ታሰሩ፤ ይፈቱ ይለቀቁ የሚሉት፡፡ እነዚህ በጋዜጠኝነት ስም የሚንቀሳቀሱ የተለየ የፖለቲካ ዓላማና አጀንዳ ይዘው ሕዝቡን ስሜታዊ በሆነ መንፈስ በማነሳሳት ሊያስከትሉ የነበረውን ጥፋት መግታት፤ ሕዝባዊና ሀገራዊ ሀላፊነትን መውጣት እንጂ በጸረ ፕሬስ ነጻነት አቋም አያስፈርጅም፡፡ እነዚህ ወገኖች ሊያስከትሉ ይችሉት ለነበረው ደም መፋሰስና እልቂት፤ የሀገር ኢኮኖሚ ውድመት ወይንም የእርስ በእርስ ግጭት መከሰትና ጥፋት ተጠያቂው ማን ነበር የሚሆነው?

በሌላው ዓለም እንደታየው ብዙ ደም ከተፋሰሰ፤ ብዙ ሺዎች ካለቁና ሀገር  ከወደመ በኋላ ምናልባት እንሲፒጄና መሰሎቻቸው የአዛኝ ቅቤ አንጓችነታቸውን "ተማጽኖና ቅስቀሳ" ለሃያላን ሃገራትና ዓለም አቀፍ ተቋማት በማሰማት በሰላም አስከባሪ ስም ጠመንጃ አስይዘው የራሳቸውን ሰዎች ሊያሰማሩ ይችላሉ፡፡ ምስቅልቅሏ በወጣ፣ ሕግና ስርዓት ባጣች

መሪና አስተዳዳሪ በሌላት ሀገር፤ የትርምሱን አጋጣሚ በመጠቀም የእነሱን ምልምሎች በተቃዋሚ ስም ያሉትን በመሾም በብቸኝነት የራሳቸውን ታላላቅ ዓለም አቀፍ ካምፓኒዎች ወደዚያች ሀገር አስከትለውም በማስገባት ለእነሱ በሚያመቻቸው መንገድና ዘዴ የሀገሪቱን የተፈጥሮ ሀብት መመዝበር ይጀምራሉ፡፡

የፕሬስ ነጻነት ዲሞክራሲ በሚል ሽፋን መሰረታዊ ተልእኮዋቸውም ይኸው ነው፡፡ ይህን ተግባራቸውን በበርካታ የመካከለኛው ምስራቅና ሌሎች ሀገራት በተደጋጋሚ ሲፈጽሙት ዓለም አይቶታል፡፡ እዳው፤ ፈተናው፤ መከራው፤ ረሀቡ ሞቱና ስደቱ፤ውርደቱ የሚወርደው፣ በሕዝቡ ላይ ነው፣ ዛሬመ እያየነው ነው፡፡ እነ ሲፒጄ፤አይፒአይ፤ አምነስቲ ኢንተርናሽናል፤ሂዩመን ራይትስ ዎች፤ኢንተርናሽናል ረሸርሰ፤ ወዘተ በተቀረጹ የጋራ ዓላማዎች፤  ግን ደግሞ የተለያየ ስም ይዘው የራሳቸውን የቁጥጥር አድማስ በዓለም ዙሪያ ለማንሰራፋት ያሰማሩአቸው የካፒታሊስቱ ዓለም ሞኖፖሊስቶችና የፋይናንሽያል ኦሊጋርኪዎች፤ጉዳይ አስጸሚና ተላላኪዎች ናቸው፡፡

እነሱ ጋዜጠኞችን በሕግ ተጠያቂ አድርጎ በማቅረብ ፍርድ ቤት እንዲወሰን የማድረጉን ሕጋዊና ሰላማዊ ሂደት ሳይሆን የሚከተሉት፤ የማይጥማቸው ከሆነ የተለየ የፈጠራ ውንጀላና ስም በመስጠት ዓለም አቀፍ ሕግን ጥሰው ሀገር የሚወሩ፤ ሕዝብን በጅትና በሚሳኤል የሚደበድቡ፤ ስንት የተለፋበትን የሀገር ኢኮኖሚ አውታር እንዳልነበር አድርገው የሚያወድሙ፤ የሚያቃጥሉ፤ የሚያነዱ ናቸው፡፡ ስለነሱ ማንም እንዲናገር የማይፈቅዱ ፍጹም አምባገነኖች ናቸው፡፤ እንደገናም ያቺ ሀገር ለማንሰራራት፤ ራሷን ለመገንባት ተመልሳ ከእነሱ ገበያ እንድትገዛ ያደርጋሉ፡፡ ይህንን የዓለም ሕዝብ ጠንቅቆ ከተረዳው ውሎ አድሯል፡፡

ሲፒጂ ራሱን የጋዜጠኛ መብት ተከራካሪ ብሎ ሰየመ እንጂ ከቶ ማን ወከለው፤ በየትኛው ሀገር ጋዜጠኞች የሚለው ጥያቄ ወደሌላ ጫፍ ይወስደናል፡፡ የእነሱን ዓላማ በቀጥታና በተዘዋዋሪ ለሚያራምዱ፤ ምስጢራዊ ግንኙነት ላላቸው፤ ምናልባትም መረጃ በማቀበል ስራ በተባባሪነት ለሚያሰሩዋቸውና በየሀገራቱ ለመለመሉዋቸው ሰዎች የህግ ተጠያቂነት ሲመጣ ድምጽ  ለማሰማት ዓለም አቀፍ ጩኸት ለመቀስቀስ ሲባል በተጠና መልኩ የተቋቋሙ ናቸው፡፡ እነዚህ ድርጅቶች ትኩረታቸው በሌላው ክፍለ ዓለም ብቻ ነው፡፡ በራሳቸው ሀገር በጋዜጠኛው ላይ ስለሚደርሰው ጫና አይናገሩም፡፡ በሌላው ዓለም በግፍ በድሮን እየተደበደበ ስለሚያልቀው ሕዝብና ጋዜጠኞችም አያወሩም፡፡ የራሳቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲሉ ወታደራዊ  ስልጠናና መሳሪያ ሰጥተው በአፍጋኒስታን ያሰማሩት ሀይል

ወደ ዓለምአቀፍ አሸባሪነት ተለውጦ ዓለምን ሲንጣት እነ ሲፒጄ፤ አምነስቲ ኢንተርናሽናል፤ ሂዩመንራይትዎች ትንፋሽ አላሉም፡፡

የእነ ሲፒጄም ሆነ የሌሎቹ ዓላማና ፍላጎት የዓለም ሀገራት ድሀ ሆነው የእነሱ የምእራባውያኑን እርዳታና እርጥባን እየጠበቁ፤ እነሱን እያመልኩ ለዝንተ ዓለም እንዲኖሩ ነው፡፡ ራሳቸውን በራሳቸው ለመቻል ከድህነት ለመውጣት አምርረው የሚታገሉ ሀገሮችን አይወዱም፡፡ ተረጂና ለማኝ ሆነው እንዲኖሩ ነው የሚፈልጉት፡፡ ከድህነት ወደ እድገት ጥላቸውና ተመንጥቃ በገሰገሰችው ቻይና ላይም ተመሳሳይ ውንጀላ ያሰሙ ነበር፣ ዛሬም ያሰማሉ፡፡ ሰሚ ግን የላቸውም፡፡

በግልጽ እንነጋገር ከተባለ የእነሲፒጄና ሌሎችም የምዕራባውያን ተቋማት በኢትዮጵያ ላይ ዘርፈ ብዙ ውንጀላ የሚያበዙት፤ለምን የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ሙሉ በሙሉ አልተቆጣጠርነውም ብለው ነው፡፡ ሁሉም ሀብትና ንብረት ወደ ግል ይዞታ ተዛውሮ የአውሮፓ ከበርቴ ባለሀብቶች በባለቤትነት እንዲይዙት ይፈልጋሉ፡፡ የኢትዮጵያ አየር መንገድ፤ ቴሌ፤ መብራት ሀይል፤ ሙሉ ለሙሉ ወደ ግል ይዞታ መዞር አለበት፣ መሬት መሸጥ መለወጥ ለግል ቱጃሮች፤ ሚሊዮነሮች፤ ቢሊዮነሮች መሰጠት አለበት ባዮች ናቸው፡፡ የእነሱ የሀብት አጋባሽነት ስሌት ሰሚ ካገኘ፤ በዚህ መልኩ ሀገርና መንግስት አለን ብሎ ለመናገር የማይቻልበት ደረጃ ላይ ይደረሳል ማለት ነው፡፡

የውጭ ባለሀብቶች እነሱ ሁሉንም የሀገሪትዋን ሀብትና መሬት ይዘው ከመሩና ካስተዳደሩ የሀገሪቱ ሕልውናስ እስከምን ድረስ ነው የሚለውም ጥያቄ ይነሳል፡፡ ይህንን እንዲያደርጉ ኢሕአዴግ አልፈቀደላቸውም፡፡ የነሲፒጄና የሌሎቹም ጬኸጻና ጫጫታ፤የፕሬስ ነጻነት አልተከበረም፤ ሰብአዊ መብት ይጣሳል፤ የዲሞክራሲ ምህዳሩ ጠቧል፤ ወዘተ እርዳታ ሰጪ ስለሆንን፤ ድሆችና ተረጂ ስለሆናችሁ እኛ የምንለው መፈጸም አለበት፤ አለበለዚያም እርዳታ እናቆማለን፤ ከፈለግንም ለእኛ አገልጋይና ታዛዥ የሆነ የፖሊሲያችን አስፈጻሚ ማስቀመጥ እንችላለን ነው የሚሉት፡፡

መንግሥት በሚያግባባን ተግባብተንና በጋራ ጥቅሞቻችን ዙሪያ በጋራ አብረን መስራት እንችላለን ነው ያላቸው፡፡ ምዕራባውያኑ ኢትዮጵያ ከቻይና ጋር ያላትንም የቀረበ ወዳጅነት አይወዱትም፡፡ ከእኛ በቀር ሌላ ሀገር ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ማየት አንፈልግም ባይ ናቸው፡፡ ይህን መወሰን ደግሞ የእነሱ መብት አይደለም፡፡ ይህም ያበሳጫቸዋል፡፡ ለዚህም መሳሪያዎቻቸው በሆኑት በእነሲፒጄ አምነስቲ ኢንተርናሽናል፤

ሂዩመንራይትዎችና ሌሎችም አማካይነት የፈረደባትን አገር በተለያዩ ክሶች ይወነጅሉአታል፡፡

በፕሬስ ነጻነት መታፈን፤ በሰብአዊ መብትረገጣ፤ የፖለቲካ ምሕዳሩ ጠቧል፤ ግድብ ልትገነባ አይገባትም፤ መሬት በውጭ ዜጎች ተይዟል፤ ነዋሪዎች ተፈናቅለዋል፤ ዓለም አቀፍ እርዳታ ያለአግባብ ስራ ላይ ውሏል ወዘተ ይህ ሁሉ በተለያየ የእነሱው አካላት እየተቀነባበረ ሃሰተኛ ክስና ውንጀላ በሂደት ሀገሪቷ የምታገኘው የውጭ እርዳታ እንዲቆም ወይንም እንዲቀንስ፤ የጀመረችው ፈጣን እድገት እንዲገታ፤ ትርምስ ውስጥ እንድትወድቅና ተመልሳም ተረጂና ተመጽዋች አገር እንድትሆን ለማድረግ የሚደረግ አፍራሽ ተልዕኮ ነው፡፡

የእኛን ፍላጎት ያልጠበቁ፤ ያላስጠበቁ፤ እንዳልናቸው የማይሆኑ የፖለቲካ ሰዎችን አስወግደን እንዳሻን የምናሽከረክራቸው ሎሌዎችን በተፈለገው ሴራ ወደ ስልጣን ማምጣት አለብን ብለው ያምናሉ፡፡ ሲፒጄም ይሄንኑ ጉዳይ አስፈጻሚነቱንና ሎሌነቱን በተደጋጋሚ እየገለጸልን ይገኛል፡፡ የሲፒጂ  እውነተኛ ገመናው ይህ ከላይ የተመለከተው ነውና በመጀመሪያ ከተላላኪነትና ከጉዳይ አስፈጻሚነት ወጥቶ ለራሱ ሙሉ ነጻነት ይኑረው፡፡ ከቅጥረኛነት ይላቀቅ፤ ስለፕሬስ ነጻነት ለመናገርና ስለሌሎች መብት ለመከራከር የራሱን ነጻነትና መብት በቅድሚያ ማስከበር አለበት እላለሁ፡፡